# ፔንስልቬንያ

## ዝግ የመጀመሪያ ደራጃ ምርጫ ስራዓት የሚከተል ግዛት ነው



### ዝግ የመጀመሪያ ደራጃ ምርጫ ስራዓት የሚከተል ግዛት ምን ማለት ነው?

በዝግ የመጀመሪያ ደረጃ መርጫ መራጭ ድምጽ መስጠት የሚችለው መራጩ ለተመዘገበበት የፖለቲካ ፓርቲ እጩዎች ብቻ ነው።

በአጠቃላይ  ምርጫ ሁሉም መራጮች ከየትኛውም ፓርቲ ጋር ቢመዘገቡም፣ ለምርጫ ለሚወዳደሩት እጩዎች ሁሉ እንዲመርጡ ይፈቀድላቸዋል።

### ከሶስተኛ ወገን ፓርቲ ጋር ወይም ካለምንም ፓርቲ ብመዘገብስ?

አንድ መራጭ ከፓርቲ ጋር ግንኙነት ከሌለው ማለትም ከየትኛውን  ፓርቲ ጋር ሳይያያዝ የተመዘገበ ቢሆን በአንደኛ ደረጃ ምርጫ ላይ ማንኛውንም እጩ ማየት አይችልም። የመጀመሪያ ደረጃ ምርጫ እያንዳንዱ ፓርቲ ለአጠቃላይ ምርጫ የሚወክለውን የመጨረሻ እጩ የሚወሰንበት ነው። ፓርቲዎችን ለአጠቃላይ ምርጫ የሚወክላቸውን የመጨረሻ እጩ ማን ሊሆን እንደሚችል መወሰን የሚችሉት የፓርቲው አባላት ብቻ ናቸው።

አንድ መራጭ በሶስተኛ ወገን ከተመዘገበ፣ እጩ ተመራጮችን ማየት የሚችለው ፓርቲው በዚያው የምርጫ ዓመት እጩ ተወዳዳሪ ካቀረበ ብቻ ነው። ሁሉም ሶስተኛ ወገኖች በሁሉም የምርጫ ዓመቶች ወይም በሁሉም ወረዳዎች እጩ ላያቀርቡ እንደሚችሉ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ነው።

ሁሉም መራጮች፣ የፓርቲ አባል ባይሆኑም በአንደኛ ደረጃ ምርጫ ላይ በምርጫ መስጫ ጥያቄዎች እና ከፓርቲ-ያልሆኑ ውድድሮች ለምሳሌ በልዩ ምርጫዎች የሚሞሉ ክፍት ቦታዎች ላይ ድምጽ መስጠት ይችላሉ። በየዓመቱ የምርጫ ጥያቄዎች እና ልዩ ምርጫዎች ላይኖሩ እንደሚችሉ ማስተዋል አስፈላጊ ነው።

በአጠቃላይ ምርጫው ሁሉም መራጮች ከየትኛውም ፓርቲ ጋር ተያይዘው ቢመዘገቡም ሆነ ያለፓርቲ ቢመዘገቡ፣ ለምርጫ የሚወዳደሩትን ማንኛውንም እጩዎች እንዲመርጡ ይፈቀድላቸዋል።

### ከየትኛው ፓርቲ ጋር እንደተመዘገብኩ እርግጠኛ አይደለሁም፡

የመራጮች ምዝገባ ሁኔታዎን ከሰር በሚገኘው አድራሻ ማረጋገጥ ይችላሉ **HTTPS://VOTE.PA.GOV/STATUS**

በዓመቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ከየትኛው ፓርቲ ጋር እንደተመዘገቡ የመለወጥ አማራጭ አለዎት። መራጮች ለውጡን በምርጫ ካርዳቸው ላይ ለማየት ከመጪው የመራጮች ምዝገባ የመጨረሻ ቀን በፊት ምዝገባቸውን መቀየር አለባቸው።

### ፓርቲዎን ለመቀየር የመጨረሻ ቀን

በዓመቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ከየትኛው ፓርቲ ጋር እንደተመዘገቡ የመለወጥ አማራጭ አለዎት። መራጮች ለውጡን በምርጫ ካርዳቸው ላይ ለማየት ከመጪው የመራጮች ምዝገባ የመጨረሻ ቀን በፊት ምዝገባቸውን መቀየር አለባቸው። **HTTPS://VOTE.PA.GOV/REGISTER**